የካቲት 30 ቀን 2004 ዓ.ም

# የበደኖ- አርባጉጉ ዕልቂትና ሠቀቀን በአባ ኒቆዲሞስ አንደበት!

ከአያልነሽ

ዕውነትና ነጋት እያደራ ይጠራል። በ1983 እስከ '84፣ '85 ዓ.ም (ኢ.ትዮ.አቆጣ) በበደኖ እና አርባጉጉ ውስጥ ስለተፈፀመው አሠቃቂ ዕልቂት ሰሞኑን በአባ ኒቆዲሞስ አንደበት ይፋ ተደረገ። አዎን! የጊዜ ጉዳይ እንጅ እውነት ተደፋፋና ልትቀር አይቻላትምና ነው። የበደኖንና የአርባጉጉ ሠቀቀን በተግባር ሲፈጸም አይተነዋልምና ነው።

ይህ አሠቃቂ የሆነው ጭፍጨፋ የተካሄደው ኢትዮጵያ ውስጥ በሐረርጌ ክ/ሀገር ወንድሙና ወገኑ ከሆነው የኦሮሞ ህዝብ ጋር ተጋብቶና ተዋልዶ በሠላምና በፍቅር ሲኖረ በነበረው፣ **በአማራው ወገኑ** ላይ የተካሄደ መሆኑ ደግሞ ጉዳዩን ይብለጥ ውስብሰብ አድርጎታል። ይሄንን አሠቃቂ ጭፍጨፋ ያካሄዱት እነማን ናቸው..... ? ብለን ብንጠየቅ ጭፍጨፋው የተካሄደው በሻዕቢያ አጋፋሪነት፣ **<u>ወያኔ ፣ ኦነግ እና ኦህዴድ</u>** እንደነበሩ የትናንት ሠቀቀናችን ትውስታ ነው።

ለኦነግ እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት የመጀመሪያው አይደለም - በ1979 ዓ.ም (ኢ.ትዮ.አቆጣ) አሶሳ በተባለው ከተማ እንዲሁ ከሻዕቢያ ጋር በመሆን ያደረገው ጭፍጨፋ ዘግናኝና ከባድ እንደነበር በጊዜው እልቂቱን የተመለከተው ሁሉ አይዘነጋውም። ታዲያ ሻዕቢያ ያኔ **«ጉሮ ወሸባዬ »** የማለት ያህል ከኦነግ ጋር ሆኖ በደስታ ሲፈንደቅ በመቅረፀ ምስል አስደግፎ የለቀቀው አሰቃቂው መረጃ ዛሬ በየሰው ቤት ማግኘት ይቻላል። እርገጥ ነው ይሄንን መረጃ ሻእቢያ ያኔም ቢሆን ለአጭር ጊዜ ብቅ አደርጎት እንደገና መሠወሩ የድርጊቱን አስቀቂነት በወቅቱ የተመለከቱት ፈረንጆችን ሁሉ ያስደነገጠ ስለነበረ ነው።

ዛሬ ደግሞ በ1983 ዓ.ም (ኢ.ትዮ አቀጣ..) ኦነግ ከአጋሮቹ ጋር ሆኖ በኢ.ትዮጵያ ምደር ምን እንደፈፀመ የሚነግረንን ታሪክ የአባ ኒቆዲሞስን ዋይታና የዓይን እማኝነት ዋቢ ያደረገውን መረጃ ትደርሱበት ዘንድ አንባቢዎች እባካችሁ ይህን ወደ ቦታው አድራሽ (ሊንክ) ተጭናችሁ (ክሊክ) በማድረግ ደግማችሁ፣ ደጋግማችሁ እንድታዳምጡት ስጠይቅ ከታላቅ አክብሮት ጋር ነው። (http://www.youtube.com/watch?v=yYWnEDgTRTY&feature=player_embedded

ይህ የአባ ኒቆዲሞስ የዓይን እማኝነት ለአሁኑ እኛ ላለንበት ትውልድ፥ **<u>አስቃቂ ጨፍጨፋ ማለት</u> <u>ምን ማለት እንደሆነ</u>** ተጨባጭና የትናንት ትኩስ ማስረጃ በእጃችን እያለ የዘመኑ **«ስልጡን ተቃዋሚ»** ነን የሚሉን ቡድኖች ግን ከዛሬ 100 እና 200 ዓመት በፊት ወደ ኋላ እየተመላለሱ እንዲያውም እነርሱም ሆነ እኛ ያልነበርንበትን ታሪክ ለመቆፈርና ለመፈለግ ይሄን ያህል ሲደክሙ የምናየው ከቶ ለምን ይሆን ....?

ደግሞስ የአባይን ገባር ወንዝ **ቡርቃን** በልጆቿ ደም በማጥለቅለቅ ትልቁን የአባይን ውሃ እስከማደፍረስ ድረስ ለምን ተጓዙ.... ? ስንል መልሱ በጣም ግለፅ ነው።እነዚህ ኃይሎች « **በነፃ አውጭነት** » ስም ጋኃድ የሆነ አሠቃቂ ጭፍጨፋ ያካሄዱትን ለማድበሰበስ መሆኑ ስይታለም የተፈታ ነው።

ይሄን ሁሉ አካሄዳቸውን ስንፈትሸው አንድ ጭብጥ ያስጨብጠናል። እነኝህ ኃይሎች ህልም አላቸው - ህልማቸውም ባልተረጋጋች ኢትዮጵያ ውሰጥ ነው እንድልባችን ሆነን መኖር የሚቻለን ብለው ከልባቸው ያምናሉ። በመሆኑም የእነርሱ ህይወት ፋታ እንዲያገኝ ኢትዮጵያ መሽመድመድ አለባት ማለት ነው።

ምፀቱ ደግሞ ይሄንን አሠቃቂ ድርጊትና መራራ እውነት የፈጸሙ ቡድኖች፣ ዛሬም ቢሆን በፈፀሙት ወንጀል ሳይፀፀቱ እንዲያውም እየተሽሞነሞኑ በዕብሪትና በማንአለብኝነት በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ <u>ያለ እኛ ማን አለ</u> ብለው ለሚጠሏት ኢትዮጵያ መሪ ተዋንያን ሆነው ብቅ ማለታቸው ነው።

ዛሬም ቢሆን ግን ከእነዚህ ቡድኖች ጀርባ **ፀረ-ኢትዮጵያ** የሆነውና በኢትዮጵያ ውድቀት ህይወት ሊዘራ የሚፈልገው ሻዕቢያም አጋፋሪ ሆኖ መሠለፉ የአደባባይ ምስጢር ነው። ታዲያ በዚህ

እንደጠራ ውሃ ቅልብጭ ብሎ በሚታይ እዉነታ ላይ የእኛ የምንላቸው ወገኖች አብረው መሠለፋቸው ሳያውቁ ነው ማለት ይቻላልን .. ? ዳሩ ግን እነኝህ ወግኖች አውቀውም ሆነ ሳይውቁ በዚህ ሠልፍ ላይ አብረው የመቆማቸው መልዕክት ትርጉሙ <u>**ለእናታቸው ሞት የመቃበር ቦታ እንደሚያዘጋጁ**</u> ዓይነት ወገኖች አስቆጥሯቸዋል።

ይሄ ብቻ አይደለም አልፎ ተርፎ እነኝህን ኃይሎች እንድንቀባላችው የሚያስገድዱንና **ተው** የሚሉንም፣ ትናንትም ሆነ ዛሬ ከእነዚህ ኃይሎች ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው **«የአማራው ህዝብ ከዬት ወደ ዬት »** የሚል መፅሀፍ በመፃፍ ነበር መሬቱን አደላድለው በተዘጋጀ ንጣፍ የበደኖና የአርባጉጉው ዕልቂት የተካሄደው።

ዛሬ፣ ይሄንን መሳይ ግፍና በደል **«በስመ ሕብረት »** ማደናገሪያ እንድንረሳው ለሚወተውቱንና የጀመርነውን ጭፍጨፋ አልጨረስንምና ታገሱን ለሚሉን ቡድኖች አሁንም አጥብቀን የምናሳሰበው፣ እባካችሁ ተረጋጉና መሬት እረግጣችሁ ቁሙ የሚል ነው። አሁንም ቢሆን ይሄ ዓይነቱ **«ፍለጠው ቁረጠው »** ዓይነት ከበሮ እየተደለቀ ያለ ለመሆኑ ዋቢ ማቅረብ አያሻም።

አባ ኒቆዲሞስ ይሄንን ተፈፀመ የተባለን ሐቅ ዛሬ ይናገሩት እንጅ ከርሳቸውም በፊት ቢሆን ቀደም ባሉት ጊዜያቶች ይሄንን የበደኖንና የአርባጉጉን ዕልቂት አስመልከቶ በርካታ ኢትዮጵያዊያን በማስረጃነት እያቀረቡ ስለ ኦነግና ስለ ኦነግ አቋም ያላቸውን ሥጋት መግለጻቸው አይዘነጋም። ይሁነና ይሄንን ስጋታቸውን ሲገልጹ የነበሩት ኢትዮጵያዊያን የኦነግ አቋም ይመርመር በማለታቸው ሳቢያ፣ እንደ **« ፀረ ኦነግ »** ተደርገው በመቆጠር ይለጠፍባቸው የነበረው የስም ማጥፋት ዘመቻን ልንዘነጋው አንችልም።

አንዳንዶችማ እንዲያውም **« ኦነግ በአብዛኛው የኦሮሞ ህዝብ የሚደገፍ ድርጅት ለመሆኑ በየጊዜው ከኢትዮጵያ በሚደረሰን መረጃ አረጋግጠናል »** እስከማለት የደረሱ እንደነበሩ ጆራችን እስኪቀደድ እንሰማው እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። ዛሬ ግን እንደዚያ ሲሉለት የነበረውን ኦነግ ትተው አሁን ደግሞ የት ላይ እንደቆሙ ስንታዘብ ወትሮም ቢሆን የእኛ ስጋትና ጥያቄ **«አካሄዳቸውን ስላዬን፣ ማንነታቸውን ለዬን »** ማለታችን እንደነበር መገንዘብ ባልተሳናቸው ነበር።

ይሁንና የአራዳ ፖለቲካ የዛሬን ለማደር እንጅ ስለ ነገ አዋዋሉ ብዙ የማይጠብብና የማይጨነቅ በመሆኑ ታዛቢ ሆነ ህዝብ ምን ይለል የሚለውን ይትባኃል የፉራ ነው ብለው **መበደል መበደል ወታደር ብድሏል-ግን አርሶ አደር ይካሳ** በማለት በህዝብና በሀገር እጣ ፋንታ ላይ ሲቀለዱ የታያሉ። ።

<u>**ኦነግ አቋሙን ይመርምር፣ ኦነግ አሁንም ከአቋሙ ፈቀቅ አላለም**</u> ስላልን የወረደብን መዓትና የተሰጠን ቅፅል ስም ተዘርዝሮ አያልቅም። ለምሳሌ ከብዙዎቹ በጥቂቱ እነኝህን ያካትታሉ - **«አክራሪዎች፣ የአማራ ነፍጠኞች፣ ያረጁ ፖለቲከኞች፣ በፖለቲካው የከሠሩ ፋራዎች፣ ትምክህተኞች፣ ...ወዘተ»**። በዚህም ሳያቆሙ እንዲህም ይላሉ - እኛ ከእነርሱ በኋላ ትናንትና ተፈጥረን ቴሌብዥን ስላለን በእኛ **«በቅናት ያበዱና የነደዱ ምቀኞች .... »** እስከ ማለትም ደርሰው የሀገራችንንና የህዝባችንን እጣ ፋንታ የሚወስነውን ፖለቲካ ሁሉ ወደታች ያወርዱታል።

ፖለቲካቸው ወደታች ሲወርድ ደግሞ ኢትዮጵያንና ህዝቧንም የሚያዩበት መነፅር የዚያኑ ያህል የወረደ ይሆናል ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ወደታች የወረደ የፖለቲካ ጨዋታ የወያኔን የጫካ ጊዜ ፖለቲካ ያስታውሰኛል። ወያኔ እንደ ወያኔ ሆኖ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ (ገና ያኔ ጫካ በነበረበት ወቅት ሁሉ) የእርሱ ፖለቲካ የመንደርና የአሉባልታ ፖለቲካ ነበርና ከዚያ ከፍ ያለ ወይም የበሰለና መሬት የረገጠ ክርክር ሲያጋጥመው ጨርቁን ይጥል እንደነበር የሚያውቁ ያውቁታል።

ለወያኔ መሬት ላይ የቆመ የፖለቲካ ክርክር ያላደገበት ነውና እንዲህ ዓይነት ነገር ሲያጋጥመው የተካነበትን የሰድብ ናዳ በማውረድ እንደእነ **ነፃነት አስፋው** የመሳሰሉ ስዶችን ያሰልፍ ነበር። በነገራችን ላይ **ነፃነት አስፋው** በኢትዮጵያዊያኖች ዘንድ ነውርና ፅያፍ የሆኑ ስድቦችን ሁሉ ትጠቀም የነበረች ሴት ነች። ያኔ ታዲያ እነ ሴኩቱሬ ጌታቸው (ሴኮ) የራዲዮ ፋና ዋና ሰዎች ነበሩና አበጀሽ !ጎሽ እያሉ ፋና

ራዲዮንን አውርደው በእነርሱ ጭንቅላትና ልክ እየሰፉ በሚተረትሩት የዘቀጠ ፖለቲካ ያጨናንቁት እንድነበር ማን ይረሳዋል ?

ለዚህም ነው ወያኔ በተራና በወረደ ስድቡ ኢሕአፓን ማሸነፍና ብዙ መራመድ እንደማይችል ሲረዳ **ኢህአፓንና ኢህአሠን** ከትግራይ ውጡልን እስከማለት ደረሰ የደረሠው። አዎን ! እርግጥ ነው ኢሕአፓ እስከአለ ወያኔ የያዘው የፖለቲካ መሥመር ኢንች ሊያራመደው እንደማይችል ቀድሞውኑ ተረድቶታል። የወያኔ ጉልበቱ ጭልፊትነቱ ነው። በመሆኑም እኛንም ልክ እንደነርሱ ጭልፊት እንድንሆን ሊመክሩን የዳዱ የዋሆችም አልታጡም ነበር። ይህ ብቻ አይደለም በእነእርሱ ዓይነት ማለትም በወያኔ ዓይነት መንገድ በጠበበ ጭንቅላትና በወረደው የመንደር ፖለቲካ ንትርካቸው ውስጥ ሊዘፍቁንም ብዙ ተጉዘው እንድነበር ከህዝብ የተሠወረ አይደለም - ደም ሁሉ የተቃባንበት ታሪክ ነውና።

## <u>ነፍጠኛና ነፍጠኝነት</u>

ህወኃት/ወያኔ ሲፈጠር ጀምሮ መጀመሪያ አፉን የፈታበት ቃል **«ነፍጠኛ»** የሚለው አባባል ነው። **« የአማራ ነፍጠኛ»** የሚለውማ የሚያቃዠውና የሚያባንነው ህልሙ ነው። ጥርሱን የነቀለበትም ይኸው ቃል በመሆኑ እስካሁንም እየቀጠለበት ይገኛል። ይሁንና ይህ እንዳለ ሁኖ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ **«ነፍጠኛ»** ያልተባለ ብሔረሰብ ቢኖር በጣም፣በጣም ጥቂቱ ነው። **«ነፍጠኛ »** ማለት ለወያኔ አልንበረከክም ያለ ሁሉ ነው። ለዚህም ነው ወያኔና መስሎቹ ከእነግሳንግሱ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ፀረ ኢትዮጵያ ሆኖ የዘመተውና የቆመው።

በወያኔ እና በግብርአበሮች አማራ በተባለው ህዝብ ላይም ይሄ ሁሉ አበሳና መከራ የሚያደርሱበትና ለዚህ ሁሉ ጣጣ የተዳረገው ኢትዮጵያዊነቱን አልከደም በማለቱ ብቻ ነው። ለነገሩማ እኛ ኢትዮጵያኖች በሙሉ ኢትዮጵያዊነታችንን መውደዳችን ምንጩ፣ ኢትዮጵያ ከምትባለው አገር በመፈጠራችን ጭምር ነው። ሁላችንም እዚህች ኢትዮጵያ ከምትባለው አገር በመፈጠራችንም ኢትዮጵያዊ ዜጎች ተብለን ለመጠራታችን ማረጋገጫ ማነነታችን ነው። ሌላም አለ። አዎ ባለ ታሪኮች ነንና በታሪካችን እና በሀገራችን ላይ ደግሞ ቀናኢ በመሆናችንም ለብዙ ፈተናዎች ተዳርገናል። ከውጭም ሆነ ከውስጥ በኢትዮጵያዊነታችን ላይ የሚወረወርብንን ቀስት ሁሉ ባለን አቅም እስካሁን ኢትዮጵያኖች በሙሉ እየመከትን እንገኛለን።

ብዙ ጊዜ ታሪክ የሌላቸው፣ አዳዲስ ታሪክ ፈጥረው ወይም ሊፈጥሩ በሚኳትኑት በእነ ስም የለሾችም **«ነፍጠኞች »** የምንባለው ያለነገር አይደለም። እንዲያው ለነገሩ ነፍጠኛ ያልሆነ ኢትዮጵያዊ ለመሆኑ ማን ነው ...? **"ያልሠለጠኑ አበሾችን ለማሰልጠን መጣን »** ባለ የሠለጠነ አውሬ ላይ ቀደም ሲል በአድዋ፣ በኋላም የዱቼ ሙሶሎኒን የጣሊያን ጦር በዓለም ፊት ድባቅ መትቶ ወደመጣበት የመለሰው ተርቡ ኢትዮጵያዊ በሞላ ነፍጡን ታጥቆ ጦሩን ሰበቆ ለመሆኑ ታሪካችን ይናገራል። ይሄም ከሆነ ነፍጠኛ የሚያስኘን አዎ ለአገራችን ቀናኢ ነንና ነፍጠኞች ነን።

እነኛ ነፍጠኛ የሆኑት አባትና እናቶቻችን፣ አያትና ቅድም አያቶቻችን ነፍጣቸውን ወልውለው፣ ጀበርናቸውን ሸብ አድርገው በመጋተራቸው የአድዋ ድል ባለቤቶች አድርገውናል። የአድዋ ድል ባለቤቶች ለመሆን የበቃነውም እኮ ነፍጠኞች በመሆናችን እንጅ ነፍጣቸውን ለጭበጥ ዝና ብለው ለወራሪው ጣሊያን የገበሩትማ በባንዳነት እራሳቸውን ስላቀረቡ፣ የደረሰባቸውን ውርደት፣ መከራና ግፍ ከእነርሱ በላይ ተናጋሪ ሊገኝ አይችለም። ለዚህም ነው.....

ምንሊክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ፣
ግብሩ እንቁላል ነበር ይሄ ሁሉ አበሻ።

ብለው ቆመን እንድንሄድ ያደርጉን አያት ቅድም አያቶቻችን ይህንን ስንኝ ተቀኝተው ያኖሩልን። በአዶልፍ ፖርልሳክም **«የአበሻ ጀብዱ »** ተብሎም ባልተፃፈልንም ነበር። ይሄ ጀብዱችን መላ ኢትዮጵያዊያንን የሚያኮራንና የምንንከባከበው ታሪካዊ ገድላችን ነው። ይሄንን ታላቅ ታሪክና ጀብዱ

ከጅምሩ ጀምሮ አንጋራውም፣አናውቀውም ብለው (ከጫካ ጀምሮ) ተፈጥመው እስካሁን የቆሙት ሻዕቢያ፤ ወያኔንና፣ አነግን፣ የመሳሰሉት ብቻ ናቸው።

እንዲያው ለነገሩ፣ ለመሆኑ ሸህ ኢሳያስ አፈውርቅ (ቂ) የሚባል ዓረብ አለ... ? አልተስምቶም፣ አልተጽፎም፣ አልተነግሮም። ዮሐንስ ለታ ወይም **«ሌንጮ »**የሚባል ኖርዌጅያዊ ፈረንጅ በፈረንጆች አገርም ገና አልተወለደም።
ባይሆን ግን ፣

***ፈረንጅ አገር ሳትሄድ ገና እዚሁ ሳለህ፣***
***የገባኸውን ቃል እንዴት ታፈርሳለህ፣***
***በፈረንጆች አገር በአውሮፓ አሜሪካ፣***
***ስለ እኛ ነበር ሰዉ የሚያውካ (ጋ)።***

የሚል የብዙዬን (ብዙነሽ በቀለ) የፍቅር ጣዕመ ዜማን ግን አጣጥመን አድገናል። ዲማ ነገዎ የሚባል ኢትዮጵያዊ የሆነ የኦሮሞ ተወላጅ እናውቃለን። ደግሞም እኮ በኦርምኛ **ዲማ** ማለት **ቀይ** ማለት እንጅ ፈረንጅ ወይም ነጭ ማለት አይደለም። ሌላም አለ። ዲማ ጊዮርጊስ የሚባል የቦታ ስም ጎጃም ክፍለ ሃገር ውስጥ እንዳለም አውቃለሁ። ዲማ ምጫራ የምትባል አንዲት መንደርም ጎንደር (ፀለምት) ውስጥ ነበረች። ትግራይም ውስጥ ዲማ የሚባል ቦታ አይታጣም፣ ሞልቷል፣ ይገኛል። ባህረነጋሽ ውስጥም እኮ ኢሣያስ እንደ አሉላ አባ ነጋ ሐውልት ደርምሶት ካለሆነ ዲማ ትገኛለች ።

እንዲህ ዓይነት ስሞች በኢትዮጵያችን ውስጥ በሽ ሲሆኑ ከዲማ የተወረሰው ዳዲሞስ የሚባል ስም ያለው ተራራችንም ሳይቀር ኢትዮጵያ ውስጥ ለመገኘቱ የዳዲሞስ ተራራ ብለን እንደ **«ቡርቃ ዝምታ"** መፅሀፍ መፃፍ አንገደድም። ወጣም ወረደ ግን እነኝህ ሁሉ መጠሪያ ስሞች የሚገኙት ኢትዮጵያ ከምትባለው አገር ውስጥ እንጅ አልባኒያ ወይም ሳውዲ አረቢያ ወይም ሱዳን ውስጥ እንዳልሆኑ 200% እርግጠኞች ነን። ጎበዝ ! ለአንድ 7 ዓመትም እኮ ሚጢጢዋ አስመሪና ቡና አምራች ነኝ ብላ ለዓለም ገቢያ አቀርባለሁ ባይ ነበረች ..... ኡ ኡ ቴ ! ምስኪን

**የሕዝብ ትግል ያሸንፋል ! የታሠሩ የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ !**
**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !**

ቸር ይግጠመን
March 9/ 2012

EthioLion.Com